# የታመሙትን መፈወስ

ካህን ዳለን ኤች ኦክስ
የአስራ ሐለቱ ሐዋሪያት ቡድን አባል

በዚህ በሚበጠበጥ አለም ዘመናት ብዙ ታማኝ ሰዎች ለመፅናናት እና ለመፈወስ ወደ ጌታ እየተመለከቱ ናቸው። ለዚህ የክህናት ባለስልጣናት ተሰብሳቢዎች የታመሙትን በህከማ፣ በጸሎት፣ እና በክህነት በረከቶች ስለመፈወስ ለመናገር እፈልጋለሁ።

I.

የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የሚገኙትን ሁሉ ጥሩ የሳይንስ እውቀትን እና ዘዴን በመጠቀም ያምናሉ። ጥሩ ምግብ መብላትን፣ መንቀሳቀስን፣ እና ዶክተሮችን ጤንነትን ደግሞ ለመመለስ እንጠቀማለን።

ለህክምና መሄድ በእምነት ጸሎት ማመናችንን እና በክህነት ስልጣን በረከቶች መመካትን የሚቃወም አይደለም። ሰው የክህነት ስልጣን በረከቶችን ሲጠይቅ ብሪገም ያንግ “መድህኒቶች ተጠቅመሀል?” ብለው ይጠይቁ ነበር። “ካህናት እጆቻቸውን እንዲጭኑብን እንፈልጋለን፣ እና ለመፈወስ እምነት አለን” ብለው አልተጠቀምንም ለሚሉትም ፕሬዘደንት ያንግ እንዲህ ብለው ይመልሳሉ፤

“ይህ ከእምነቴ ጋር የሚጋጭ ነው። ከታመምንና ጌታ እንዲባርከን ፣ እና በደህንነት ወንጌል እውቀታችን መሰረት መደረግ የሚገባውን ሁሉ እንዲያደርግልን ከጠየቅን፣ ጌታ በሬትን ሳላርስ እና ዘሩን ሳልዘራ ስንዴን እና እህሌን ጌታ እንዲያሳድግልኝ እንደምጠይቅ ነው። በእውቀቴ የሚመጣውን የህክምና ዘዴ መጠቀም፣ እና ከዛም የሰማይ አባቴን ሰውነቴን ለመፈወስ የማደርገውን እንዲቀድስ መጠየቅ ትክክል እንደሆነ ይታየኛል።”

በእምነት መጸለይን ወይም ለመፈወስ የክህነት ስልጣን በረከት መስጠትን ሌሎች ዜዴዎችን እስካደረግን ድረስ አንጠብቅም። በአደጋዎች ጊዜ ጸሎት እና በረከቶች በመጀመሪያ ይደረጋሉ። በብዙ ጊዜ ሁሉንም ጥረቶች በአንድ ጊዜ እንሞክራቸዋለን። ይህም “ሁልጊዜ ጸልዩ” እና ሁሉም ነገሮች በጥበብ እና በስርዓት ይደረጉ የሚለውን የቅዱስ መጻህፍት ምክርን ይህም ይከተላል።

II.

በብቻ፣ ወይም በቤቶቻችን ውስጥ ወይም በ ጸሎት ቤቶች ውስጥ የሚደረግ የእምነት ጸሎት የታመመን የመፈወስ ውጤታማ ለመሆን ይችላል። ብዙ ቅዱስ መጻህፍቶች ግለሰብን ለመፈወስ ስለእምነት ሀይል ይናገራሉ። ሐዋሪያው ያዕቆብ “ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች” ብሏል (ያዕቆብ 5፡16)። ሴቷ ኢየሱስን ነክታ በተፈወሰች ጊዜ፣ እንዲህ ብሏታል፣ “እምነትሽ አድኖሻል”። እንደዚህም መፅሐፈ ሞርሞን ጌታ “በሀይል በሰዎች ልጆች እምነት መሰረት ይሰራል” በማለት ያስተምራል።

በቅርብ በተጠየቀው ጥያቄ ከ10 አሜሪካዊያን 8ቶቹ "በጥንት ጊዜ እንደነበረው አይነት ታምራት አሁንም እንደሚገኝ" እንደሚያምኑ ታውቋል። ከእነዚህም አንድ ሶስተኞቹ "መለኮታዊ መፈወስ አጋጥሞናል ወይም አይተናል" ብልዋል። ብዙ የኋለኛ ቀ ቅዱስና የታመሙትን በእምነት ሀይል መፈወስን ለማየት አጋጣሚዎች አግኝተዋል። እምነት ባላቸው በሌሎች ቤተክርስትያኖችም ይህን ምሳሌዎች እንሰማለን። በቴክሳስ ጋዜጣ አንድ ሰው እንደዚህ አይነት ታምራትን ገልጿል። አንድ የአምስት አመት ሴት ልጅ ትኩሳት ይዟት መተንፈስ አስቸግሯት ነበር፣ ወላጆቿ ወደ ሆስፒታል በፍጥነት ወሰዷት። በእዚያ በደረሰች ጊዜ ኩላሊቷ እና ሳንባዋ መስራት አቁመው ነበር እና ትኩሳቷም 107 ነበር፣ እና ሰውነቷም ቀይ ሆኖ በቁስሎች ተሸፍኖ ነበር። ዶክተሮቹ በማይታወቅ ህመም እየሞተች ነች አሉ። ወደ ቤተሰቧ እና ጓደኞች ይህ ዜና ሲደርስ፣ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች መጸለይ ጀመሩ እና በቤተክርስትያኗም ውስጥ ልዩ የጸሎት ስብሰባ ተደረገ። በድንገትም ከሞት የተንጠለጠለችው ከአንድ ሳምንት በኋላ ከሆስፒታል ወጣች። አያቷም እንዲህ ብለው ጻፉ፣ "እግዚአብሔር ጸሎትን እንደሚመልስ እና ታምራትን እንደሚሰራ የምታሳውቅ ነች።"

በእውነትም መፅሐፈ ሞርሞን እንዲህ ያስተምራል፣ እግዚአብሔር "በእርሱ ለሚያምኑት ሁሉ እራሱን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይገልፃል፤ አዎን፣ ለሁሉም መንግስታት፣ ወገን፣ ቋንቋና ህዝብ እንደ እምነታቸው በሰው ልጆች መካከል አስደናቂ ተአምራትን፣ ምልክትን፣ እና ድንቅ ነገርን ይሰራል።"

III.

የመልከጸዴክ የክህነት ባለስልጣን ለሆኑት ጎልማሳዎች እና ይህን ስልጣን በቅርብ ለሚቀበሉ ወጣት ወንዶች ስናገር፣ የክህነት ስልጣን ሀይልን በመጠቀም ለመፈወስ የምንጠቀምበትን በረከት ላይ አተኩራለሁ። ይህ የክህነት ስልጣን ሀይል አለን እና እርሱንም ለመጠቀም መዘጋጀት አለብን። በዚህ በገንዘብ ችግር እና መአት በሚጨምሩበት ጊዜ ይህን ሀይል ከወደፊት በላይ ለመጠቀም እንደሚያስፈልገን እናያለን።

ብዙ ቅዱስ መጻህፍት የጌታ አገልጋዮች "እጃቸውን በታመሙት ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ" ብለው ያስተምራሉ። ታምራት የሚደርሰው የክህነት ስልጣን ሀይልን የታመሙትን ለመባረክ ስንጠቀምበት ነው። እነዚህ ታምራቶች እኔንም አጋጥመውኛል። እንደ ወጣትነቴ እና ጎልማሳነቴ በቅዱስ መጻህፍት ላይ እንደተጻፉት ታምራቶች አጋጥመውኛል እና ብዙዎቻችሁም አጋጥሟችኋውል።

የታመሙትን ለመባረክ የክህነት ስልጣንን ለመጠቀም አምስት ክፍሎች አሉ፤ መቀባት፣ የተቀባውን ማተም፣ እምነት፣ የበረከት ቃላት፣ እና የጌታ ፈቃድ።

መቀባት

የብሉይ ኪዳን በዘይት መቀባት በክህነት ስልጣን የሚደረገው መባረክ ክፍል እንደሆነ በየጊዜው ያሳያል። መቀባት ለመቀደስ ነው ተብሎ ታውጇል፣ እና በዚህ ቅዱስ ስራ ምክንያት ከሰማይ እንደሚፈሰው በረከት ምሳሌም ሊሆን ይችላል።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የኢየሱስ ሐዋሪያት “የታመሙትን ዘይት እየቀቡ ፈወሱአቸው” ብሎ እናነባለን። የያዕቆብ መፅሐፍም ከክህነት ስልጣን በመባረክ መፈወስ ጋር መቀባት ያለውን ግንኙነት ያስተምራል።

“ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ሽምግሌዎች ወደ እርሱ ይጥራ፤ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት።”

“የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል ጌታም ያስነሣዋል፤ ኃጢአትንም ሠርቶ እንደ ሆነ ይሰረይለታል።”

*መቀባትን ማተም*

በመልከጼደቅ የክህነት ስልጣን ማንም ሰው ሲቀባ፣ የተቀባውም በዚህ ስልጣን ይታተማል። አንድን ነገር ማተም ማለት ማረጋገጥ፣ እና ለአላማው እንዲተሳሰር ማድረግ ማለት ነው። ካህናት የታመመን ሰው ሲወቡ እና የቀቡትን ሲያትሙ፣ ለታመመው ሰው ጌታ በረከት እንዲያፈስ የሰማይ መስኮቶችን ይከፍታሉ። ፕሬዘደንት ብሪገም ያንግ እንዳስተማሩት፤

“በታመመው ላይ እጆቼን ስጭን፣ የእግዚአብሔር መፈወሻ ሀይል እና ተፅዕኖ ከእኔ በኩል አልፎ ወደ በሽተኛው እንዲሄድ እና በሽታውን እንደሚለቅ እጠብቃለሁ…።

“ስንዘጋጅ፣ በጌታ ፊት ቅዱስ እቃ ስንሆን፣ ወደበሽተኛው የሁሉን ቻይ ሀይል በሚባርኳቸው ሰዎች በኩል አልፎ ይሄዳል፣ እና በሽተኞችም ደህና ይሆናሉ…።”

ምንም እንኳን በክህነት ስልጣን የተባረኩ ሰዎች እንደተፈወሱ ብናውቅም፣ የአሁን ራዕያት “ስለእነዚህ ነገሮች በጉራ አታውሩ፣ ወይም በአለም በፊትም አትናገሩበት፤ እነዚህ ነገሮች ለጥቅማችሁና ለደህንነታችሁ የተሰጧችሁ ነገሮች ናቸውና” በመባል ስለተጠነቀቅን በህዝባዊ ስብሰባዎች ስለእነዚህ መፈወስ ሁልጊዜም አንነጋገርባቸውም።

*እምነት*

እምነት በሰማይ ሀይል ለመፈወስ አስፈላጊ ነው። መፅሐፈ ሞርሞን “በሰው ልጆች መካከል እምነት ከሌለ እግዚአብሔር በመካከላቸው ተአምር መስራት አይችልም፤” ብሎ ያስተምራል። የታመሙትን ስለመባረክ በሰጡት ንግግር ፕሬዘደንት ኪምባል እንዲህ ብለዋል።

“የእምነት አስፈላጊነት በዝልቀት ይገመታል። የታመመው እና ቤተሰቡ የሚባርኩት ወንድሞች እንዳሉአቸው ተስፋ በሚያደርጉት የክህነት ስልጣን ሀይል እና የመፈወስ ስጦታዎች ላይ ተስፋቸውን ይጥላሉ፣ ግን ታላቁ ሀላፊነት ያለበት በሚባረከው ላይ ነው።…ግለሰቡ የሚያውቅ እና እቅመ አዳም ያለው ከሆነ፣ ዋናው ክፍሉም የግለሰቡ እምነት ነው።. ‘እምነትሽ ፈወሰሽ’ የሚለው ቃላት በጌታ በየጊዜው ተደጋግሞ ነበር:

ፕሬዘደንት ኪምባል "ሁልጊዜም በረከትን መስጠት የእምነት ማጣት ምልክት ወይም እምነት የመገንባትን ሀላፊነት ከታመመው ወደ ካህናት መቀየር ሊሆንም ይችላል" በማለት ሀሳብ አቅርበው ነበር። የክህነት ስልጣን በረከት ስለተቀበለች ታማኝ ሴት ተናግረው ነበር። በሚቀጥለው ቀን በረከት እንደምትፈልግ ስትጠየቅ፣ እንዲህም መለሰች "ተቀብቼ ተባርኬአለሁ። ስነስርዓቱ ተከናውኗል። አሁን በረከቴን በእምነት የመቀበል ሀላፊነት የእኔ ነው።"

የበረከት ቃላት

የክህነት ስልጣን በረከት ሌላው ክፍልም ቅባትን ካተሙ በኋላ ካህናት የሚናገሩት የበረከት ቃላት ናቸው። እነዚህም ቃላት አስፈላጊ ቢሆኑም መሰረታዊ አይደሉም እና በቤተክርስትያን መዝገብ ላይ አይጻፉም። እንደ ፔትሪያርክ በረከት አይነት አንዳንድ በረከቶች የሚናገሩት ቃላቶች የበረከቶች ዋና ግፍል ናቸው። ነገር ግን በመፈወሻ በረከት የበረከቱ ሌሎች ክፍሎች፣ እንዲሁም መቀባት፣ መታተም፣ እምነት፣ እና የጌታ ፈቃድ፣ አስፈላጊ ናቸው።

በረከት የሚሰጠው ሰው ከጌታ መንፈስ ጋር የሚስማማ ሆኖየጌታን ፈቃድ አውቆ በበረከት ቃላቶች የጌታን ፈቃድ የሚገልፅ እንደሚሆን ተስፋ ይኖረናል። ብሪገም ያንግ የክህነት ባለስልጣንን እንዳስተማሯቸው፤ "የጌታ ቃል ለእናንተ ሲናገር እና የጌታ አስተሳሰብ ሲገለፅላችሁ ለማወቅ ብቁለመሆን የመኖር መብት እና ሀላፊነት አለባችሁ።" ይህ ሲሆን የተናገራችሁት በረከት በእውነትም በታምራትም ይሟላል። በአንዳንድ ምርጥ ጊዜዎች የመፈወስ በረከትን ስሰጥ ያ የተረጋገጠ መነሳሻ አጋጥሞኛል እና የጌታን ፍላጎት እየተናገርኩኝ እንዳለሁ አውቃለሁ። ነገር ግን የመፈወስ በረከት እንደሚሰጡት ሌሎችም ምን ቃላት መጠቀም እንዳለብኝ እጠራጠር ነበር። በተላያዩ ምክንያቶች ካህናት በመንፈስ መነሳሳት ያላቸው አጋጣሚዎች ሊጨምሩም ሊቀንሱም ይችላሉ።በረከት የሚሰጥ ማንም ካህን ለታመመው ሰው እንዲደርስለት በሚፈልገው መገፋፋቱ አይቀርም። እነዚህ እና ሌሎች ስጋዊ ውድቀቶች በምንናገራቸው ቃላቶች ላይ ተፅዕኖ አላቸው።

የምንናገራቸው ቃላት ግን በበረከቱ የመፈወስ ውጤታ ላይ እስከዚህም አስፈላጊነት የላቸውም። እምነት ብቁ ከሆነ እና የጌታ ፍላጎት ከሆነ፣ የታመመው ሰው የሚባርከው ሰው ቃላቶችንቢላቸውም ባይላቸውም ይፈወሳል ወይም ይባረካል። በሚባርከው ሰው ልምድ ማጣት ወይም በግል ፍላጎት ምክንያት ጌታ በግለሰቡ እምነት መሰረት ለመስጠት ከሚፈቅደው በላይ ትእዛዛትን ወይም የበረከት ቃላትን ከሰጠ፣ እነዚህ ቃላቶች አይሟሉም። በዚህም ምክንያት ማንም ካህን ምን ማለት እንደሚገባው ስለማያውቅ በመፈወስ በረከት ለመሳተፍ መፍራት የለበትም። በመፈወስ በረከት ጊዜ የተናገሩት ቃላት ያስተምራሉ እናም የሚሰሟቸውን ሰዎች እምነትንም ያጠናክራሉ፣ ነገር ግን የበረከቱ ውጤታ በእምነት እና በጌታ ፈቃድ ላይ የሚመካ ነው እንጂ በረከት በሚሰጠው ካህን ቃላት ልአይ የሚመካ አይደለም።

የጌታ ፍላጎት

ወጣት እና ሽማግሌ ወንዶች አሁን ለምለው እባካችሁ ትኩረት ስጡት። የማይጠራጠረውን የእግዚአብሔር የክህነት ስልጣን ሀይልን ስንጠቀምበት እና የእምነት ጸሎትን ለማሳመጥ እና ለመመለስ የገባውን የተስፋ ቃል ስናከብር፣ የክህነት ስልጣኑ ከሆነው ጌታ ፈቃድ እና ፍላጎት ተቃራኒ የሆነ ውጤታ እምነት እና የመፈወስ ሀይል ሊያመጡ እንደማይችሉ አስታውሱ። ይህም መሰረታዊ መመሪያ ካህናት

እጆቻቸውን አሳርፈው እንዲፈውሱ በታዘዙበት ራዕይ ውስጥ ይገኛሉ። "ለመፈወስ በእኔ እምነት ያለው፣ እና ለሞት ያልተመደበው፣ ይፈወሳል" ብሏል ጌታ። እንደዚህም በሌላ ራዕይ ጌታ "አንድ ሰው በእግዚአብሔር ፈቃድ በኩል ሲጠይቅ፣ ...ይህም እንደጠየቀው ይደረጋል" በማለት አውጇል።

የጌታን መለኮታዊ ሀይል የሚጠቀሙበት የጌታ አገልጋዮችም በምንም ጉዳይ የሰውየው መፈወስ የጌታ ፈቃድ ካልሆነ ሰውየው እንዲፈወስ የሚያደርግ የክህነት ስልጣን በረከት ለመስጠት አይችሉም።

እንደ እግዚአብሔር ልጆች፣ የእርሱን ታላቅ ፍቅር እና እርሱ ለእኛ ምን ነገሮች እንደሚጠቅሙን ያለውን እውቀት በማወቅ በእርሱ እምነት ይኑረን። የወንጌሉ የመጀመሪያው መሰረት በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ነው። በበሽታ ምክንያት ስለሞተች አንድ ወጣት ልጅ የአጎቴ ልጅ በተናገረው እምነት አለኝ። በመጀመሪያ ያስደነቁኝ ከዛም ያስተማሩኝን ቃላት ተናገረ፤ "እንሷ መሞቷ የጌታ ፈቃድ እንደሆነ አውቃለሁ። ህክምና ነበራት፣ የክህነት ስልጣን በረከት ተሰጥቷታል፣ በቤተመቅደስ የጸሎት መዝገብ ላይም ስሟ ለበረ። ጤንነትን እንድታገኝም ብዙ መቶ ጸሎቶች ተደርጎላት ነበር። እርሷን ወደቤት ለመውሰድ የጌታ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ቤተሰብ ውስጥ እርሷን ለመፈወስ ብቁ እምነት እንዳለ አውቃለሁ።" በወጣትነቷ ሴት ልጁ በካንሰር የሞተችበት አባት ቃልም እንደዚህ አይነት እምነት አለኝ። "እንዲህም አለ፣ "እምነታችን የሚመካው በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት እንጂ በውጤታ የሚመካ አይደለም።" እነዚህ ትምህርቶች እውነት ናቸው። ለምናፈቅራቸው መፈወስ የምንችለውን እናደርጋለን፣ እና ከዛም ለውጤታውም ጌታን እናምናለን።

ስለእግዚአብሔር የክህነት ስልጣን ሀይል፣ ስለእምነት ጸሎት ሀይል፣ እና ስለእነዚህ መሰረታዊ መመሪያ እውነትነት እመሰክራለሁ። ከሁሉም በላይ ከሞት መነሳቱ የህያውነት ማረጋገጫ እና የኃጥያት ክፍያው ለዘለአለም ህይወት እድል ስለሰጠን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እመሰክራለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፣ አሜን።